የእውነት ፍለጋ ተከታታይ ቅፅ 3

# መልዕክቱ አንድ ነው !

ዶ/ር. ናጂ እ . አርፋጅ

ትርጉም፡ ተሺቴ ሮቤ

# መታሰቢያ

## ለነዚያ  በትህትና፤በታማኝነትና ሰፋ ባለ አዕምሮ እዉነትን ለሚፈልጉት !

# ማውጫ


የቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች 4

ቀጥታ ወደ ቁምነገር 5

አንድ ፈጣሪ ብቻ በመጽሐፍ ቅዱስ ብሉይ ኪዳን 15

አንድ ፈጣሪ ብቻ በመጽሐፍ ቅዱስ በአዲስ ኪዳን 17

አንድ ፈጣሪ ብቻ በቁርዓን 19

ማጠቃለያ 21

## የቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች :

1. ይህ ‘አንድ መልዕክት ብቻ’ ማለት ምንድነው?

2. መጽሐፍ ቅዱስስ ስለ እርሱ ምን ይላል ?

3. ቅዱስ ቁርዓንስ ስለ እርሱ ምን ይላል ?

4. የርስዎስ አስተያየት ምንድነው ?

## ቀጥታ ወደ ቁምነገር

አዳም ከተፈጠረ በኃላ በሰው ልጆች ታሪክ ዉስጥ አንድ መሠረታዊ መልዕክት ብቻ በተደጋጋሚ ለሰው ልጆች ይተላለፍ ነበር፡፡

ይኸውም የሰው ልጆችን ለማስገንዘብና ወደ ቀጥተኛ ጐዳና ለመመለስ ብዙ ነብያት እና መልዕክተኞች አዳምን፣ኖህን፣አብረሃምን፣ሙሴን፣ ኢየሱስንና ሙሀመድን ጨምሮ ይህንን አንድ መልዕክት እንድያስተላልፉ በአንድ እውነተኛ አምላክ ተልኮዋል፡፡

***እውነተኛው አምላክ አንድ ብቻ ነው፡፡እርሱን ብቻ አምልክ ትዕዛዛትንም ጠብቅ፡፡***

•

## እውነተኛዉ አምላክ፣ፈጣሪዉ

ላከ:

እንድያደርሱ፡

--------- አዳም — አምላክ አንድ ነው

--------- ኖህ — አምላክ አንድ ነው

--------- አብረሃም — አምላክ አንድ ነው

--------- ሙሴ — አምላክ አንድ ነው

--------- ኢየሱስ — አምላክ አንድ ነው

--------- ሙሀመድ — አምላክ አንድ ነው ።

አምላክ እነዚህን ዋና ዋና ነብያትና እንዲሁም ሌሎችም ብዙ መልዕክተኞችን ብዙ ሥራዎችንና ተልዕኮዎችን እንድያከናዉኑ ልኳል፡፡ከነዚህም ዉስጥ፤

1) መመሪያዉን ከአምላክ ተቀብሎ ለሰዎች እንድያስተላልፉ፡፡

2) አምላክ አንድ ብቻ መሆኑን መልዕክት እንድያስተላልፉ፡፡

3) ለሕዝባቸዉ ምሳሌ እንድሆኑ፡፡

4) ተከታዮቻቸዉን አስፈላጊ ኃይማኖት እና ግብረ ገባዊ ትምህርት እንድያስተምሩ፡፡

5) ሕዝቦቻቸዉን የአምላክን ፍራቻና የርሱን ትዕዛዛት እንድጠብቁ ማስጠንቀቅ

6) እነዚያን የተጣመሙትን ፣አምላክን ያልታዘዙትንና ጣዖታትን የሚያመልኩትን ወደ ቀጥተኛ መንገድ እንድመሩ፡፡

7) የመጨረሻዉን ቀን ለሰዎች እንድነግሩ እና ወደ ጀነትና ወደ ጀሐነም የሚያስገቡትን መንገዶች እንድያሳዉቁ፡፡

እነዚያን ነብያቶችና መልዕከተኞች የፈጠራቸዉና የላካቸዉም ይኸው አንድ አምላክ ነዉ፡፡እርሱም የሁሉም የሰዉ ዘሮች፣የሁሉም እንስሳትና የሁሉም ነገሮች ፈጣሪ ነዉ፡፡ ይህ እዉነተኛ አምላክ ብቻ ነዉ ህዋዉንና በዉስጡ ያሉትን ነገሮች ሁሉ የፈጠረዉ፡፡እርሱ የህይወት፣ ሞትና ከሞት በኋላ ያለዉን ህይወት ፈጣሪ ነዉ፡፡

የዚህ እዉነተኛ አምላክ አንድነት(የፈጣሪዉ) በአይሁዶች፣ በክርስቲያኖች፣ በሙስሊሞችና በሌሎችም ቅዱሳን መጻሕፍት ዉስጥ በግልፅ የተረጋገጠና በቀላሉ ለማወቅም የሚቻል ነዉ፡፡

የአምላክን ደረጃ በቁርዓንና በመጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ በትህትና እና በቅንነት በማጥናት ብቻ እዉነት ፈላጊዉ የእዉነተኛዉን አምላክ ደረጃ በቀላሉ ሊገነዘብ ይችላል፡፡

እውነተኛውን አምላክ ከሌሎች አማልክት የሚለዩት አንዳንድ ደረጃዎች ወይንም ባህሪያት፡

- ይህ እውነተኛ አምላክ ፈጣሪ እንጂ ፍጡር አይደለም ፡፡
- ይህ እውነተኛ አምላክ አንድ ብቻ ነው። ሦስት ወይንም ከዚያ በላይ አይደለም፡፡ አቻና አምሳያ የለውም፡፡
- ይህ እውነተኛ አምላክ አይታይም፤በዚህ አለም ህይወት ውስጥ ማንም አያየውም፡፡ በአካልም በሌሎች ተመስሎ አይገለጽም፡፡
- ይህ እውነተኛ አምላክ ዘለዓለማዊ ነው፡፡ አይሞትም አይለወጥም፡፡
- ይህ እውነተኛ አምላክ ከሌሎች ፍላጎቶች ነፃ ነው፡፡ እንደ እናት ሚስት እና ልጅ አያስፈልጉትም ወይንም እንደ ምግብ መጠጥና እርዳታ አያስፈልጉትም፡፡ ነገር ግን ሌሎች ለመኖር ይህንን እውነተኛ አምላክ ይፈልጉታል፡፡
- ይህ እውነተኛ አምላክ ባህሪው ልዩ ነው፡፡ ማንም እንደርሱ ያለ የለም፡፡ የማንኛውም ሰው ወይንም እንስሳ ባህሪ ለርሱ አይገባም፡ ፡

እነዚህን መስፈርቶችና ባህርያት እንዲሁም ሌሎችንም ለርሱ(ለፈጣሪ) ብቻ የሚገቡትን በመጠቀም ስለርሱ መመርመርና የውሸት አማልክትን መቃወም እንችላለን፡፡

አሁን እላይ ስለተጠቀሰው ወደ ዋናው ጉዳይ መልዒክቱ አንድ ብቻ ልመለስና የአምላክን አንድነት የሚያረጋግጡ መጽሀፍ ቅዱሳዊና ቁርዓናዊ አንቀጾችን ልጥቀስ፡፡ ነገር ግን ከዚያ በፊት ይህንን ሀሳብ ከናንተ ጋር ለመጋራት እፈልጋለሁ፡፡

‹‹አምላክ አንድ ብቻ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ እኛም ሙስሊሞች በዚሁ አንድ አምላክ እናምናለን ስንል አንዳንድ ክርስቲያኖች ሊደነቁ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ነጥቡ ምንድነው?››

ይሁን እንጂ ብዙ የክርስትና እምነት ማስረጃዎችን በማንበብ፣ በማጥናትና ከብዙ ክርስቲያኖችም ጋር ባካሄድኩት ውይይቶች ላይ በመመርኮዝ ይህ አንድ አምላክ የሚከተሉትን የሚያካትት ነው ብሎ እንደሚያምኑ ለመረዳት ችያለሁ፡፡

1 - አምላክ ፡ አባት
2 - አምላክ ፡ ልጅ
3 - አምላክ ፡ መንፈስ ቅዱስ

ስለሆነም በስሜት ህዋሳታችንና በቀላል ሎጂክ ላይ በመመስረት ማንኛውም ትሁትና ታማኝ እውነት ፈላጊ ይህንን መጠየቅ ይችላል፡፡

- አምላክ አንድ ነው በምትሉበት ጊዜ ምን ማለታችሁ ነው በሌላ በኩል ሦስትዮሻዊ አምላኮችን እያመለከታችሁ?
- አላምክ አንድ ከሦስት ውስጥ ወይንስ ሦስት ከአንድ (1 በ 3 ወይንስ 3 በ 1?)

ከዚህ በተጨማሪ በክርስቲያኖቹ የኃይማኖት ትምህርት መሠረት እነዚህ ሦስት አምላኮች የተለያዩ መለያዎች ፣ ምስሎች ፣ ተግባራትና የሥራ ድርሻዎች አሏቸው፡፡

1 - አምላክ ፡ አባት = *ፈጣሪ*
2 - አምላክ ፡ ልጅ = አዳኝ
3 - አምላክ ፡ መንፈስ ቅዱስ = አጽናኝ

ለመሆኑ ኢየሱስ አምላክ ልጅ (የአምላክ ልጅ) እውነተኛ አምላክና የአምላክ አካል ከሆነ ይህ አባባል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጠቀሰው ማንም ሰው አምላክን ማየት አይችልም፤ድምፁንም አይሰማም ከሚለው ጋር አይቃረንምን?

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል

- የላከኝ አብም እርሱ ስለ እኔ መስክሮአል። ድምፁን ከቶ አልሰማችሁም፥ መልኩንም አላያችሁም፤ (ዮሐንስ 5: 37)

... አንድ ሰው እንኳ አላየውም ሊያይም አይቻለውም፤ .... (1ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 6: 16)

❖ ደግሞም ሰው አይቶኝ አይድንምና ፊቴን ማየት አይቻልህም አለ። (**ኦሪት ዘፀአት** 33: 20)

በነዚህና በሌሎችም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶች መሰረት በትህትናና በታማኝነት የምጠይቃችሁ ነገር ‹‹ኢየሱስ አምላክ ነው የሚለውን ቀኖና እና ማንም ሰው እንኳን አምላክን ያየም ሆነ ድምፁንም የሰማ የለም የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምስክርነት እንዴት ነው የምናስታርቀው?››

→ በርሱ ዘመን የነበሩት አይሁዶች ፣ የርሱ ቤተሰቦችና ተከታዮቹም እየሱስን (አምላካዊውን ወልድ አንዳንዶች እንደሚያመኑት) አላዩትምን?

→ እውነተኛውን አምላክ በተመለከተ ለመሆኑ የሆነ ሚስጥር ወይንም የተደበቀ አላማ አለንን?

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እውነተኛው አምላክ አጥብቆ ይመሰክራል፡፡

"በስውር ወይም በጨለማ ምድር ስፍራ አልተናገርሁም፤ ለያዕቆብ ዘር በከንቱ ፈልጉኝ አላልሁም፤ እኔ እግዚአብሔር ጽድቅን እናገራለሁ ቅንንም አወራለሁ።" (**ትንቢተ ኢሳይያስ** 45: 19)

ስለሆነም እውነቱ ምንድነው? እባክዎን ደግሞ ደጋግሞ ይህንን ጥቅስ እያነበቡ ያስቡበት!

አሁን የእውነተኛውን አምላክ ፍለጋ ጉዟችንንበመጽሐፍ ቅዱስና በቁርዓን ውስጥ እንጀምር፡፡

ከዚህ ጉዞ በኋላና ይህንን መጽሔት ምክንያታዊ በመሆን፣ በትህትና፣ በታማኝነትና በማስተንተን በተለይም ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ጥቅሶች ካነበቡ በኋላ የርስዎን አስተያየት ወይንም አመለካከት ለመስማት እፈልጋለው፡፡

**በተቻለ መጠን ነፃ በመሆን ጥቅሶቹን እንዳሉ ያለ ምንም አስተያየት ለማስቀመጥ ሞክሪያለሁኝ፡፡ እባክዎን የሚከተሉትን ጥቅሶች በጥንቃቄ ሎጂካዊ(ምክንያታዊ)በመሆን ያለ** አንዳች ቅድመ ሀሳብ ያንብቡ፡፡

**እውነተኛው አንድ አምላክ በመጽሐፍ ቅዱስ (ብሉይ ኪዳን) ፡-**

- እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው፤ (**ኦሪት ዘዳግም** 6: 4)

- እግዚአብሔር የሕይወትን መንፈስ አንድ አድርጎ ጠብቆልን የለምን **?** ......
(ትንቢተ ሚልክያ 2: 15)

- ታውቁና ታምኑብኝ ዘንድ እኔም እንደሆንሁ ታስተውሉ ዘንድ፥ እናንተ የመረጥሁትም ባሪያዎቸ ምስክሮቼ ናችሁ ይላል እግዚአብሔር፤ ከእኔ በፊት አምላክ አልተሠራም ከእኔም በኋላ አይሆንም። እኔ፥ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፥ ከእኔ ሌላም የሚያድን የለም። (ትንቢተ ኢሳይያስ 43: 10-11)

- … እኔ ፊተኛ ነኝ እኔም ኋለኛ ነኝ፥ ከእኔ ሌላም አምላክ የለም። (**ትንቢተ ኢሳይያስ** 44: 6)

- … ከእኔም በቀር ሌላ አምላክ የለም፤ እኔ ጻድቅ አምላክና መድኃኒት ነኝ፥ ከእኔም በቀር ማንም የለም።… እኔ አምላክ ነኝና፥ ከእኔም በቀር ሌላ የለምና ወደ እኔ ዘወር በሉ ትድኑማላችሁ።… ጉልበት ሁሉ ለእኔ ይንበረከካል፥ ምላስም ሁሉ በእኔ ይምላል ብዬ በራሴ ምያለሁ። (**ትንቢተ ኢሳይያስ** 45: 21-23)

**እነዚህ አንዳንድ ከብሉይ ኪዳን የተወሰዱ ጥቅሶች ናቸው፡፡**

*እርሶስ ሌሎች ተመሳሳይ ጥቅሶችን ያስታውሳሉ?*

**እውነተኛው አንድ አምላክ በመጽሐፍ ቅዱስ (አዲስ ኪዳን) ፡**

- እነሆም፥ አንድ ሰው ቀርቦ መምህር ሆይ፥ የዘላለምን ሕይወት እንዳገኝ ምን መልካም ነገር ላድርግ? አለው። እርሱም ስለ መልካም ነገር ለምን ትጠይቀኛለህ? መልካም የሆነ አንዱ ብቻ ነው፤ወደ ሕይወት መግባት ብትወድ ግን ትእዛዛቱን ጠብቅ አለው። (የማቴዎስ ወንጌል 19: 16-17, )

- እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት።(**የዮሐንስ ወንጌል** 17: 3)
- .... ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአልና አለው። (የማቴዎስ ወንጌል 4: 10)

- ...እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው፥ (**የማርቆስ ወንጌል** 12: 29)

- አንድ እግዚአብሔር አለና፥ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፥ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ (1ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 2: 5)

**እርሶስ ሌላ የሚያስታውሱት ስለ**
አንድ አምላክ ብቻ የተጠቀሰ ካለ?(ሦስት አይደለም)

# እውነተኛ አንድ አምላክ በቁርዓን

- በል «እርሱ አላህ አንድ ነው፡፡ **(1)** «አላህ (የሁሉ) መጠጊያ ነው፡፡ **(2)**«አልወለደም፤ አልተወለደምም፡፡ **(3)** «ለእርሱም አንድም ብጤ የለውም፡፡»**(4)** (112: 1-4)

- ....እነሆ ከእኔ ሌላ አምላክ የለምና ተገዙኝ.... (21: 25)

- እነዚያ «አላህ የሦስት ሦስተኛ ነው» ያሉ በእርግጥ ካዱ፡፡ ከአምላክም አንድ አምላክ እንጂ ሌላ የለም፡፡ ከሚሉትም ነገር ባይከለከሉ ከነሱ እነዚያን የካዱትን አሳማሚ ቅጣት በእርግጥ ይነካቸዋል፡፡ (5: 73)

- ....ከአላህ ጋር ሌላ አምላክ አለን? ግን አብዛኞቻቸው አያውቁም፡፡ (27: 61)

- ...ከአላህ ጋር ሌላ አምላክ አለን? አላህ (በእርሱ) ከሚያጋሩዋቸው ሁሉ ላቀ፡፡ (27: 63)

...ከአላህ ጋር ሌላ አምላክ አለን? «እውነተኞች እንደኾናችሁ፤ አስረጃችሁን አምጡ» በላቸው፡፡ (27: 64)

ይህ የአምላክ አንድነት መልእክት በአረብኛ ተውሂድ የሚባለዉ የቁርዓን አስፈላጊውና ዋና ርእሰ ጉዳይ ነው፡፡

## ማጠቃለያ

እነዚህ አንቀጾችና ሌሎችም መሰል በመቶዎች የሚቆጠሩ ተመሳሳይ ጥቃቅን ማስረጃዎች በመጽሐፍ ቅዱስ እና በቁርዓን ውስጥ ያሉ ሲሆን እነርሱም እውነተኛው አምላክ አንድ ብቻ መሆኑን በዚሁ አንድ ዘላለማዊ መልዕክት ያረጋግጣሉ፡፡

እናንተ የምድር ዳርቻ ሁሉ፥ እኔ አምላክ ነኝና፥ ከእኔም በቀር ሌላ የለምና ወደ እኔ ዘወር በሉ ትድኑማላችሁ።( ትንቢተ ኢሳይያስ 45፡22)

መጽሐፍ ቅዱስ አምላክ አንድ መሆኑን ማረጋገጥ ብቻ ሰይሆን እውነተኛው አምላክ ፈጣሪም አዳኝም እንደሆነ ይገልፃል፡፡

... ከእኔ በፊት አምላክ አልተሠራም ከእኔም በኋላ አይሆንም።. . . እኔ እግዚአብሔር ነኝ፥ ከእኔ ሌላም የሚያድን የለም።(ትንቢተ ኢሳይያስ 43፡10-11 )

ስለሆነም በዚህ ማረጋገጫ መሰረት ሌሎች አማልክት የተሰኙት ኢየሱስ ፣ መንፈስ ቅዱስ ፣ ቢራህማ ፣ ቪሽኑ ፣ ክርሽና ወይንም ቡድሃ አምላኮች አይደሉም፡፡ ምክንቱም የእውነተኛ አምላክ መገለጫዎችም ስላልሆኑ፡፡

በነዚህ የውሸት እምነቶች ነበር አይሁዶች ሌሎች አማልክት ባመለኩ ጊዜ ‹‹የጌታ ቁጣ ያቃጠላቸው››(**ኦሪት ዘሁልቅ** 25:3) በዝሁ ተመሳሳይ ሁኔታ ነበር ሙሴም ወርቃማውን የጥጃ ምስል የደመሰሰው፡፡

“እስራኤልም ብዔልፌጎርን ተከተለ፤ የእግዚአብሔርም ቍጣ በእስራኤል ላይ ነደደ።” (**ኦሪት ዘሁልቅ** 25: 3)

በሌላ በኩል የመጀመሪያዎቹ አሀዳውያን ክርስቲያን ህብረተሰብም ለቶርች (ግርፋት) እና ለስደት የበቁት፡፡ የኢየሱስን አሃዳዊ ትምህርት በጳውሎስ የፈጠራ ስላሴ ለመለወጥ እንቢ በማለታቸው ነው፡፡

ለማጠቃለል ያህል ሁሉም የአላህ ነቢያት አደም ፣ ኑህ ፣ አብራሃም ፣ ሙሴ ፣ ኢየሱስና ሙሐመድን ጨምሮ የተላኩት በአንድ አምላክ በፈጣሪ አንድ መልዕክት ብቻ እንዲያደርሱ ነው፡፡

እውነተኛው አምላክ አንድ ብቻ ነው ፣ እርሱን ብቻ አምልኩ ፣ ትዕዛዛቱንም ጠብቁ፡፡

እነዚህም ነቢያትና መልዕክተኞች የሰበኩት አንድ መልዕክት ብቻ ስለሆነ ሀይማኖታቸውም አንድ መሆን አለበት፡፡ ስለዚህ የነዚያ ነቢያትና መልዕክተኞች ሀይማኖት ምንድነው?

ለአምላክ እራስን ማስገዛት (መታዘዝ) የነዚህ ነቢያት መልዕክት ይዘት ነው፡፡ ይህም ቃል እራስን ማስገዛት (መታዘዝ) ማለት በአረብኛ እስላም ማለት ነው፡፡

እስላም የሁሉም ነብያትና መልዕክተኞች ሀይማኖት መሆኑን ቁርዓን ያረጋግጣል፡፡ እነዚህ ቁርዓናዊ ጭብጦች ከመጽሐፍ ቅዱስም ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ ይህም በአላህ ፍቃድ በሚቀጥለው መጽሔት ውስጥ ይቀርባል፡፡

በመሰረቱ መድህንን ለማግኘት እላይ የጠቀስነውን መልዕክት በፍቃደኝነትና በልበ ሙሉነት መቀበልና ማመን አለብን፡፡

የሆነ ሆኖም ይህንን ማድረግ ብቻ በቂ አይደለም፡፡ በሁሉም የአምላክ እውነተኛ ነብያት ሙሐመድን ጨምሮ ማመንና የነርሱን እውነተኛ መመሪያና ትምህርቶችን መቀበልና መከተል አለብን፡፡ ይህም ለዘላለማዊ ህይወትና ደስታ ዋና መግቢያ በር ነው፡፡

**ስለዚህ በታማኝነት እውነት ፈላጊ ከሆኑና መዳንን የሚወዱ ከሆነ ይህንን ጉዳይ** አሁኑኑ ከማርፈድዎ በፊት ቢገመግሙ ይሻላል! ከመሞትዎ በፊት! በቅርብ ሊሆን ይችላል! ማን ያውቃል?

አንድ ተጨማሪ ነገር . . .

*መልዕክቱ አንድ ነው !*

## *የመጨረሻ ሀሳብ!*

*እነዚያ እውነትን በመፈለግ ትሁቶች ፣ ታማኞች ፣ ጥንቁቆች ፣ ግልጽነት ያላቸውና ሰፋ ያለ አዕምሮ ያላቸው የሆኑት ስለዚህ መልዕክት ምክንያታዊ የሆነ አስተሳሰብ ያላቸው እንደዚህ ያሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ ይችላሉ፡-*

→ ስለዚህ እውነቱ ምንድነው?

→ እኔስ ምን ማድረግ እችላለሁ?

**እርሶም በትህትና** በእውነተኛ አምላክ (አላህ) ማመንና በርሱም የመጨረሻ መልዕክተኛ በማመን የሚከተለውን መመስከር ይችላሉ፡፡

*እኔ እመሰክራለው ፡ ከአንድ አላህ በስተቀር በሀቅ የሚመለክ የለም፡፡ ሙሐመድም የአላህ መልዕክተኛ ነው፡፡*

- ይህም ምስክር ለዘላለማዊ ህይወት የመጀመሪያው እርምጃና ለጀነት መግቢያም እውነተኛ ቁልፍ ነው፡፡

*ይህንን መንገድ ለመቀበል ከወሰኑ የሙስሊም ጓደኛዎን ፣ በአቅራቢያዎ ያለውን እስላማዊ ማዕከልና እኔን (የዚህ መጽሐፍ ደራሲን) ማነጋገር ይችላሉ፡፡ እኔም ለመርዳት በጣም ደስተኛ ነኝ፡፡*

***እውን ማድረግ ይችላሉ!***

## ስለ እስልምና ሐይማኖት ዋና ዋና አባባሎችና ማብራሪያዎች በአጭሩ፡፡

### አላህ
የአንድ እውነተኛ አምላክ ትክክለኛ መጠሪያ ስም ነው፡፡ አላህ የሁሉም የሰው ልጆች (የአየሁዶች ፣ የክርስቲያኖች ፣ የሙስሊሞች ፣ የሂንዱዎች ወዘተ ... እውነተኛ አምላክ ነው፡፡

### ሙሐመድ
የአንድ እውነተኛ አምላክ (አላህ) የመጨረሻ ነብይ ነው፡፡

### ኢስላም
እራስን ለፈጣሪ ፍላጎት ማስገዛት ሲሆን ይህም ፈጣሪ እውነተኛ አምላክ አላህ ብቻ ነው፡፡ አንድ ሰው እውነተኛውን ደስታና የአእምሮ ሰላም ሊጎናፀፍ የሚችለው ለእውነተኛው አምላክ እጅ በመስጠትና እርሱን በመታዘዝ ነው፡፡

### ሙስሊም
ማንኛውም እራሱን ለአንድ እውነተኛ አምላክ (ፈጣሪ) የሚያስገዛ ሁሉ ሙስሊም ይባላል፡፡

## ቁርዓን

በነቢዩ ሙሐመድ ላይ የወረደው የአምላክ ቃል ነው፡
፡

## Writings by the Author

- What is His Nature?
- Just One Message!
- Have You Discovered Its Real Beauty?

**Useful web sites on Islam:**

http://www.islamreligion.com

http://www.islamhouse.com

http://www.edialogue.org

http://newmuslimacademy.org

http://en.islamway.net

http://www.sultan.org

**For further information, questions, suggestions, *feedback*, or reactions, Please feel free to contact the author:**

**Dr. Naji Arfaj**

**E-mail: abctruth@hotmail.com**

**Website: www.360itsrealbeauty.com**

**Tel +96655913113**
**P. O. Box 418 Hofuf, Ahsa**

**31982 KSA**